www.chilot.me

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፺፱
አዲስ አበባ ታህሳስ ፬ ቀን ፪ሺ፲፪

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No. 99
ADDIS ABABA December 14th, 2019

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፬፻፶፱/፪ሺ፲፪ ዓ.ም

የመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽንን እንደገና ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ……..……ገጽ ፲፪ሺ፶፫

Content

Regulation No.459/2019

Army Foundation Re-Establishment Council of Ministers Regulation …………………….Page 12053

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፶፱/፪ሺ፲፪**

**የመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺፯/፪ሺ፲፩ አንቀጽ ፴፬ መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩.አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ “የመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽንን እንደገና ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፶፱/፪ሺ፲፪” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION NO. 459/2019**

**ARMY FOUNDATION ESTABLISHMENT COUNCIL OF MINISTERS REGULATION**

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 34 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 1097/2018.

1. **ShortTitle**

This Regulation may be cited as the “Army foundation Re-Establishment Council of Ministers Regulation No. 459/ 2019”.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

**፪.ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

፩/“በክብር የተሰናበተ አባል” ማለት በዲሲፕሊን ወይም በወንጀል ጥፋት ከተሰናበተ በስተቀር በማንኛውም ሁኔታ የተሰናበተ የሠራዊት አባል ነው፡፡

፪/“አገልግሎት” ማለት በፋውንዴሽኑ ስር በሚተዳደሩ ተቋማት አማካኝነት የሚሰጥ ልዩ ልዩ ማህበራዊ፤ኢኮኖሚያዊ፤ስፖርታዊ፤ መዝናኛ፣ እና የመሳሰለ አቅርቦት ወይም አገልግሎት ነው፡፡

፫/”ምርት” ማለት በፋውንዴሽኑ ስር በሚተዳደሩ ፋብሪካዎች የሚመረት ወይም በግዥ ለፋውንዴሽኑ አባላት የሚቀርብ ማናቸውም አይነት እቃ ነው፤

፬/”ቤተሰብ” ማለት የፋውንዴሽኑ አባል ባል ወይም ሚስት እና ከአስራ ስምንት ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ናቸው፡፡

፭/”ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር” ማለት የመከላከያ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡

፮/በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

**፫.መቋቋም**

፩/የመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽን (ከዚህ በኋላ “ፋውንዴሽን” እየተባለ የሚጠራ) የህግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ እንደገና ተቋቁሟል፡፡

፪/ ፋውንዴሽኑ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

**፬.ዋና መስሪያ ቤት**

የፋውንዴሽኑ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ስፍራ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል፡፡

**2. Definitions**

In this Regulation, unless the context requires otherwise:

1/ "Ex-members of the army” means those who are discharged from the regular army service in any condition other than disciplinary or criminal offence.

2/ "Service" means a service supplied by the organizations that is provided by the army Foundation like social, economic, sports and recreations.

3/ "Product” means any material that is manufactured or bought by the organizations provided by an army Foundation.

4/ "Family" means the husband, wife and children under eighteen Years of the members of Army Foundation.

5/ Ministry or Minister means Ministry or Minister of National Defense.

6/ Any expression in the Masculine gender includes the Feminine.

**3. Establishment**

1/ Army Foundation (hereinafter the "Foundation") is hereby re - established as an Autonomous Institution having its own Legal Personality.

2/ The Foundation shall be accountable to the Ministry.

**4. Head Office**

The Foundation shall have its Head office in Addis Ababa and may have Branches elsewhere as may be necessary.

www.chilot.me


## ፭. ዓላማዎች

ፋውንዴሽኑ_የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

፩/የሠራዊት አባላትን ኑሮ ለማሻሻል፣ የሚረዱ ተግባራት ማከናወን፤

፪/ የሚኒስቴሩን ገፅታና ሳቢነት ማጎልበት፣

፫/የሠራዊቱን ሞራል ለመጠበቅና፣ ለማጎልበት የሚያግዙ ልዩ ልዩ ተግባራት ማከናወን፤

፬/የሠራዊቱን የግዳጅ አፈፃፀም ብቃት በማረጋገጥና በመጠበቅ ረገድ የላቀ አስተዋጽኦ ማበርከት፤

፭/የፋውንዴሽኑን አባላት ግንኙነትና የትብብር አድማስ ማስፋት፣

## ፮.አባልነት

፩/ የፋውንዴሽኑ አባል መሆን የሚችሉት የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ) በስራ ላይ ያለ የመከላከያ ሠራዊት አባል፤

ለ) ከመከላከያ ሠራዊት በክብር የተሰናበተ አባል፣

ሐ) ቋሚ የፋውንዴሽኑ ሲቪል ሰራተኛ፣

መ) የመከላከያ ሠራዊት እና የሚኒስቴሩ የቋሚ ሲቪል ሰራተኛ ቤተሰብ፣

ሠ)ፋውንዴሽኑ አባል እንዲሆኑ የሚፈቅድላቸው ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች፡፡

ረ የፋውዴሽኑ አባላት መብትና ግዴታ ቦርዱ በሚያወጣው የፋዉንዴሽኑ የዉስጥ ደንብ ይወሰናል፤

## 5. Objectives of the Foundation

The Foundation shall have the following objectives:

1/ Provide service and facilities required to meet the needs of members of the army and to improve their quality of life;

2/ Improve the image and Attractiveness of the Ministry;

3/ Carry out activities intended to maintain and enhance high standard of morale for the army by providing service and facilities;

4/ Contribute to ensure and maintain the army to carry out task or mission;

5/ Strengthen the Unity and interaction members of the Foundation.

## 6. Membership

1/ Membership of the Foundation shall be open to:

a) Regular army members;

b) Ex- members of the army who are honorably discharged;

c) Permanent Civil Servants of the Foundation;

d) Families of members of the defense force and permanent Civil Servants;

e) Other category of persons as prescribed by the Foundation;

f) Rights and Obligations shall be specified by law of the Foundation to be issued by the Board.

www.chilot.me



## ፯.ተግባራትና የህግ ችሎታ

ፋውንዴሽኑ የሚከተሉት ተግባራትና ችሎታ ይኖሩታል፡-

፩/ ለፋውንዴሽኑ አባላት የተመረጡ ምርቶችና አገልግሎቶችን ማቅረብ፣ ወይም እንዲቀርቡ ማድረግ፤

፪/ የሠራዊት አባላት እና ቋሚ ሲቪል ሰራተኞች የመኖሪያ ቤት ባለቤት ለማድረግ የሚያስችሉ ተግባራት ማከናወን፣

፫/ የብድርና ቁጠባ ማህበር በማቋቋም በአነስተኛ ወለድ የብድር አገልግሎት መስጠት፣

፬/ ለፋውንዴሽኑ አባላት ማህበራዊ አገልግሎቶችን፣ የስፖርት ማዘውተሪያ፣ የመዝናኛ እና የመሳሰሉትን አገልግሎቶች መስጠት፣

፭/ የኢትዮጵያን የፋይናንስ ህጎችና ጥናትን መሰረት በማድረግ ዓላማውን ለማሳካት በሚያስችሉ የባንክ ስራን ጨምሮ በተለያዩ የኢንቨስትመንት መስኮች መሳተፍ፣

፮/ ከሠራዊቱ በክብር የተሰናበቱ አባላትን መልሶ ለማቋቋም የሚደግፉ ሥራዎች ማከናወን፤

፯/ የፋውንዴሽኑን የፋይናንስ አቅም የሚያጎለብቱ ልዩ ልዩ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ስራዎችን ማከናወን፣

፰/ በሰላም አስከባሪነት ለማገልገል ወደ ሌሎች አገራት ለሚሄዱ የሠራዊቱ አባላት በአገር ውስጥ የውጪ ምንዛሪ የባንክ ሂሳብ እንዲኖራቸው ማመቻቸት፣

## 7. Functions and Legal Capacity

The Foundation shall have the Functions and Legal capacity to:

1/ Supply or make to be supplied selective products and services to the army members;

2/ Undertake activities that make the Army members and Permanent Civil Servants owners of residence house;

3/ Provide saving and loan service on concessionary interest rates by establishing saving and loan association;

4/ Provide social services, sport and other recreational services to the army members of the Foundation;

5/ Based on assessment and in accordance with Ethiopian financial laws, engage in different investment opportunities necessary for the attainment of its objectives, including banking sector;

6/ Engage in supportive activities for the re-establishment of ex-members of the army;

7/ Engage in different fund raising activities that can Strengthen the financial capacity of the Foundation;

8/ Facilitate the opening of Foreign Currency saving account at domestic Commercial Banks for army members engaged in peace keeping service abroad;

፱/ የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በስሙ መክሰስና መከሰስ፣

፲/ ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎችን ተዛማጅ ስራዎችን ማከናወን፡፡

**፰·<u>አደረጃጀት</u>**

ፋውንዴሽኑ፡-

፩/ ቦርድ፣

፪/ ዋና የስራ አስፈፃሚ እና ምክትል ዋና ስራ አስፈፃሚዎች እና ፣

፫/ አስፈላጊው ሰራተኞች ይኖሩታል፡፡

**፱.<u>የቦርዱ አባላት</u>**

፩/ የፋውንዴሽኑ ቦርድ አባላት ከመከላከያና አግባብ ካላቸው አካላት ተውጣጥተው በሚኒስቴሩ ይሰየማሉ፡፡ ቁጥራቸውም ከአምስት (፭) እስከ ሰባት(፯) ይሆናል፡፡

፪/ የፋዉንዴሽኑ ሥራ አስፈጻሚ ዳይሬክተር ድምጽ የማይሰጥ አባልና ፀሐፊ ይሆናል፡፡

**፲.<u>የቦርድ አባላት የስራ ዘመን</u>**

የቦርድ አባላት የስራ ዘመን ሁለት ዓመታት ይሆናል፡፡ ሆኖም አባላቱ ለቀጣይ የአገልግሎት ዘመን እንደገና ሊመረጡ ይችላሉ፡፡

**፲፩.<u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>**

የፋውንዴሽኑ ቦርድ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የዚህን ደንብ አፈፃፀም በሚገባ ይከታተላል፤ ያረጋግጣል፣

፪/ የፋውንዴሽኑን የስራ እንቅስቃሴና እድገት በተመለከተ አጠቃላይ አቅጣጫ ይሰጣል፣

፫/ የፋውንዴሽኑን ዓመታዊ በጀትና የስራ እቅድ ያፀድቃል አፈፃፀሙን ይከታተላል፣

9/ Own property, enter in to contracts, sue and be sued in its own name;

10/ Engage in any related activities necessary for the attainment of its objectives.

**8. <u>Organization</u>**

The Foundation shall have:

1. A Board,

2/ An Executive Director; Deputy Chief Executive Officers; and

3/ The Necessary staff.

**9. <u>Members of the Board</u>**

1/ Members of the Board including the Chairperson shall be appointed by the Ministry to be drawn from the defense and other relevant organs. Their number shall be five (5) up to seven (7) members.

2/ The Executive Director of member and Secretary of the board having no voting Power.

**10. <u>Tenure of Board members</u>**

The Board members shall serve for two years; provided. However, that the members may be re-elected for subsequent tenures.

**11. <u>Powers and Duties of the Board</u>**

The Board shall have the following Powers and Duties:

1/ Follow up and ensure the proper implementation of this Regulation ;

2/ Give the overall directions to the activities and growth of the army Foundation;

3/ Approve annual budgets and programs of the Foundation;

፬/ የፋውንዴሽኑ የአሰራር መመርያ ያወጣል ፣ያፀድቃል፡፡

፭/ የፋውንዴሽኑን ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት እና የሚወገዱ ንብረቶችን ያፀድቃል ፣የውጪ ኦዲተር ይሾማል፣

፮/ ፋውንዴሽኑ የሚያደርጋቸውን ማንኛውንም አይነት ብድሮች ያፀድቃል፣

፯/ፋውንዴሽኑ የሚያቀርበውን የኢንቨስትመንት ፍላጎት ከዓላማው አንፃር መርምሮ ያፀድቃል፣

**፲፪.የቦርዱ ስብሰባዎች**

፩/ የቦርዱ መደበኛ ስብሰባ በየሶስት ወሩ አንድ ጊዜ ይደረጋል ፣ሆኖም በሰብሳቢው ሲጠራ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊደረግ ይችላል፡፡

፪/ በቦርዱ ስብሰባ ላይ ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ-ጉባዔ ይሆናል፡፡

፫/ የቦርዱ ውሳኔ የሚተላለፈው በስብሰባው ከተገኙ አባላት አብላጫ ድምፅ ሲደገፍ ይሆናል፡፡ ሆኖም ድምፅ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፡፡

**፲፫.የፋዉንዴሽኑ የሥራ አስፈጻሚ ስልጣንና ተግባር**

፩/ከቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ አቅጣጫ መሰረት የፋውንዴሽኑን ስራዎች ያቅዳል፣ ይመራል ፣ያስተዳድራል ፣ ይቆጣጠራል፡፡

፪/የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ) የቦርዱ ውሳኔዎች ስራ ላይ ያዉላል ፣ ዉሳኔዎቹ በትክክል ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል ፣ያረጋግጣል፣

4/ Issue Directives for army Foundation and approve it;

5/ Approve annual financial reports of the Foundation and voidable properties and appoint external auditors;

6/ Approve any loan ;

7/ Approve the investment possibilities by considering the objectives of the army Foundation;

**12. Meeting of the Board**

1/ The Board shall hold its regular meetings once every three months; provided, however, that extraordinary meeting of the board may be held at any time when called by the Chair Person.

2/ The presence of the majority of the members at a meeting of the Board shall constitute a quorum.

3/ Any decision of the Board shall be passed by a majority of votes of members present at a meeting; in case of a tie, the Chairperson shall have a casting vote.

**13. Powers and Duties of the Executive Director**

1/ The Executive Director shall plan, direct and administer the activities of the Foundation based on the general direction given by the Board.

2/ Without prejudice to the generality of sub-article ( 1) of this article:-

a) Implement the decision of the Board , Follow up and ensure the proper implementation of decisions;

www.chilot.me



ለ) አግባብ ባለው ሕግና ቦርዱ በሚያፀድቀው የዉስጥ ደንብ መሰረት የፋውንዴሽኑን ሰራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፣

ሐ) የፋውንዴሽኑን ዓመታዊ በጀትና የስራ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል ፣ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣

መ) ለፋውንዴሽኑ በተፈቀደው በጀትና የስራ ፕሮግራም መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣

ሠ) ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ፋውንዴሽኑን ይወክላል፣

ረ) የፋውንዴሽኑ ገቢ በወቅቱ መሰብሰቡንና በፋውንዴሽኑ የባንክ ሂሳብ ገቢ መደረጉን ያረጋግጣል፣

ሰ) ስለፋውንዴሽኑ ዓላማና ስለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ለማስተዋወቅ የሕዝብ ግንኙነት ስራዎች መከናወናቸውን ያረጋግጣል፣

ሸ) የቦርዱ ስብሰባዎች ሪኮርዶች በአግባቡ እንዲያዙና እንዲጠበቁ ያደርጋል፣

ቀ) የፋውንዴሽኑን የስራ ክንውንና የፋይናንስ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፣

በ) ፋውንዴሽኑን የሚገልጽ ዓርማ በማሰራትና በቦርድ እንዲፀድቅ በማድረግ ተግባራዊ ያደርጋል፣

ተ) ከቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፡፡

b) Employ, terminate and administer the employees of the Foundation in accordance with applicable laws and by laws to be issued by the Board;

c) Prepare and submit to the Board the annual budget and work program of the Foundation and implement the same upon approval;

d) Effect expenditure in accordance with the approved budget and work program of the Foundation;

e) Represent the Foundation in all its dealing with third parties;

f) Follow up the timely collection of accrued revenues of the Foundation and deposit same in the Foundation's bank account;

g) Ensure the undertaking of public relation activities to popularize the objectives and services of the Foundation;

h) Ensure that the meeting of the board are properly recorded and maintained;

i) Prepare and submit to the Board the performance and financial reports of the Foundation;

j) Prepare ,submit and approve the logo that describe army Foundation by the Board ;

k) Perform such other Duties as may be given to him by the Board.

፪/ለፋውንዴሽኑ ስራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ስልጣንና ተግባሩን በከፊል አግባብነት ላላቸው የፋውንዴሽኑ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

**፲፬.<u>የፋውንዴሽኑ የገቢ ምንጭ</u>**

፩/ ፋውንዴሽኑ የሚከተሉት የገቢ ምንጮች ይኖሩታል፡-

ሀ) ከአባላት የሚሰበሰብ መዋጮ፣

ለ) ፋውንዴሽኑ ከሚያቀርባቸው ምርቶችና አገልግሎቶች የሚገኝ ገቢ፣

ሐ) ከፋውንዴሽኑ ኢንቨስትመንቶች የሚገኘው ገቢ፣

መ) አግባብነት ባለው ሕግ መሰረት ሚኒስቴሩ ከተለያዩ የገቢ ምንጭ፣ ከሚያገኘው ገቢ የሚመድበው የድጎማ ገንዘብ፣

ሠ) ከተለያዩ ምንጮች የሚገኝ ማናቸውም ስጦታ ወይም እርዳታ፣

ረ) ከመንግስት የሚገኝ ድጋፍ፤

ሰ) ፋውንዴሽኑ ከሚያከናውናቸው የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራሞች የሚገኝ ገቢ፤

ሸ) ከፋዉንዴሽኑ ቁጠባና ብድር የሚገኝ ገቢ፣

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ከተመለከቱት ምንጮች የሚሰበሰበው ገቢ በፋውንዴሽኑ ስም በተከፈተ የባንክ ሂሳብ ተቀማጭ ተደርጎ ለፋውንዴሽኑ ዓላማ ማስፈፀሚያ ይውላል፡፡

**፲፭. <u>የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር</u>**

ፋዉንዴሽኑን በሚመለከት ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡፡

፩/ የፋውንዴሽኑ ዓላማዎች በአግባቡ እየተፈፀሙ መሆኑን ያረጋግጣል፤ ተገቢ የሆነ ድጋፍና፣ ክትትል ያደርጋል፣

2/ The Executive Director may delegate part of his Powers and Duties to other Officers and Staff of the Agency to the extent necessary for the effective discharge of the activities of the Foundation.

**14. <u>Sources of Income of the Foundation</u>**

1. The foundation shall have the following source of income:

   a) Membership Fees;
   b) Income generated from the supply of products and services of the Foundation;
   c) Income generated from investments of the foundation;
   d) Subsidy funds allocated by the ministry found from different source of income in accordance with relevant laws ;
   e) Donations and assistance secured from anybody;
   f) Support from Government;
   g) Income generated from Telethons undertaken by the Foundation;
   h) Income from saving and loan of the Foundation;

2. The funds collected from the sources specified under sub-article (1) of this article shall be deposited in a bank account opened in the name of the Foundation and shall be utilized to finance the operations of the Foundation.

**15. <u>Power and Duties of the Ministry</u>:**

The Ministry shall have the following Powers and Duties in relation to the Foundation:

1/ Follow up, ensure and supervise the proper implementation of the Foundation's Objectives,

www.chilot.me



፪/ ሰብሳቢዉን ጨምሮ የፋውንዴሽኑ ቦርድ አባላትን ይሰይማል፣

፫/ የፋውንዴሽኑን ዋና ስራ አስፈጻሚ ይሾማል፤ ያሰናብታል፣

፬/ ለዋና ስራ አስፈጻሚ ዳይሬክተር ተጠሪ በሆኑ የስራ መደቦች ላይ የሚመደቡትን የስራ ኃላፊዎች ምደባ እና ስንብት ያጸድቃል፡፡

**፲፮.<u>የበጀት ዓመት</u>**

የፋውንዴሽኑ የበጀት ዓመት በየዓመቱ ሐምሌ ፩ ቀን ጀምሮ በሚቀጥለው ዓመት ሰኔ ፴ ቀን ያበቃል፡፡

**፲፯.<u>የሂሳብ መዛግብት</u>**

፩/ ፋውንዴሽኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡

፪/ የፋውንዴሽኑ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየዓመቱ በውጭ ኦዲተሮች ይመረመራሉ፡፡

**፲፰.<u>የኃላፊነት መጠን</u>**

ፋውንዴሽኑ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

**፲፱. <u>ፋውንዴሽኑ የሚቆይበት ጊዜ</u>**

ፋውንዴሽኑ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

2/ Appoint the Foundation's Board members including the Chair Person;

3/ Appointing and dismiss the Foundation's chief Executive Director;

4/ Approve the assignment of Officers to posts directly accountable to the Executive Director of the Foundation.

**16. <u>Fiscal Year</u>**

The Fiscal Year of the Foundation shall begin on the 1st Day of Hamle of each Year and end on the 30th Day of Sene of the following year.

**17. <u>Books of Accounts</u>**

1/ The Foundation shall keep accurate and complete books of accounts

2/ The Book of accounts and financial documents of the Foundation shall be audited annually by external auditors.

**18. <u>Extent of Liability</u>**

The Foundation shall not be liable beyond its total assets.

**19. <u>Duration of the Foundation</u>**

The Foundation is established for an indefinite duration.

www.chilot.me



**፳.የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች**

፩/የመከላከያ ፋውንዴሽን ደንብ ቁጥር ፩፻፸፱/፪ሺ፪ ዓ.ም በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

፪/ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**፳፩.ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ፣ ታህሳስ ፬ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም**

**ዶ/ር አብይ አሕመድ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

**20. Repealed and Inapplicable Laws**

1/ Defense Foundation Establishment Regulation No. 179/2002 E.C is hereby repealed;

2/ All Directives and Customary Practices which are inconsistent with this Regulation shall not apply on matters under this Regulation.

**21. Effective Date**

This Regulation shall enter in to force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 14th Day of December, 2019.**

**ABIY AHMED (DR.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**